ከገብሩ አድጋቦ ታህሳስ 24 2000
ሚላኖ-ጣሊያን

# “ኢሕአፓን ማፍረስ?!”

## “መደየን ዕንጂ መኮነን፤ዕንደ ኩንቲ ዕንደ ጋኔን
## መዋቅር፤መዋቅር፤መዋቅር፤ የትም የትም መዋቅር
## በየብስ፤ባየር፤በባሕር”

“ግንባርህን አሳያቸው!”
በፀጋዬ ገብረመድህን (ደብተራው)
ቋራ 1977 ዓም

“መደየን ዕንጂ መኮነን፤
ዕንደ ኩንቲ ዕንደ ጋኔን
በምን ስሌት? በምን ሚዛን?
ተመካኝቶ በአምባገነን
የሰማዕት ደም ማምከን።

ትግል በቃኝ ዕግሬን አውጪኝ
ስጋውን ወዳድ አቀንቃኝ
አደረገው ባጣ ቆየኝ?!
የትም የትም ዞሮ
የራሱን ኑሮ ኖሮ
ቀፈቱን ወጥሮ
ስጋውን አወፍሮ
ከማንም የትም አድሮ
አሳቢ ተኮነ ዘንድሮ

በታኞች! አንጃዎች!
የት ነበራቹ?
መቸ ታያቹ
ለስጋቹ ያደራቹ
ለጥፋት ያ-ደ-ራ-ቹ
ካናዳ-ቺካጎ ቦድናቹ
ኤል-ኤንም ጨምራቹ
አትላንታ ላይ ሰረጋቹ
ዲሲ ላይ ፈነዳቹ::

“መደየን ዕንጂ መኮነን፤
ዕንደ ኩንቲ ዕንደ ጋኔን
በምን ስሌት? በምን ሚዛን?
ተመካኝቶ በአምባገነን
የሰማዕት ደም ማምከን።

በጠራራ ፀሐይ
በባንዳ፤አንጃ፤አድር ባይ
በፋሺስት ዱለቻ አባይ
በከተማ ባደባባይ
ሙሺራው ወንድሜ ሲሰረይ
ደሙ ሆኖ ያገር ሲሳይ
ስጋው ሆኖ ያገር ሲሳይ
እምዬ ስትል ዋይ! ዋይ!
ለማዝለቅ የወንድሜን ራዕይ
ጦር መስበቅ ነው በኢሕአፓ ላይ?::

“መደየን ዕንጂ መኮነን፤
ዕንደ ኩንቲ ዕንደ ጋኔን
በምን ስሌት? በምን ሚዛን?
ተመካኝቶ በአምባገነን
የሰማዕት ደም ማምከን።

ጠላት ባራት አቅጣጫ
እያሳጣ መግቢያ መውጫ
ያባት ቤት ሆኖ መራገጫ
የግፈኛ መፈንጫ
ጥግ ጠፍቶ ማድፈጫ
ቀዳዳ ማምለጫ
ተኩኖ ዓይን ና ናጫ
ሚስጢር ካልተነገረኝ
ኢሕአፓን አፈረስነ
እነ አሉላ አሉነ::

"መደየን ዕንጂ መኮነን፤
ዕንደ ኩንቲ ዕንደ ጋኔን
በምን ስሌት? በምን ሚዛን?
ተመካኝቶ በአምባገነን
የሰማዕት ደም ማምከን።

ለግፈኛ መወገኛ
መሆን ሲገባ ቀንኛ
ለበጋሻው ዉቃቢ. . .
. . . አበጅቶ መጋረኛ
የክህደት መስገኛ
የብተና ማርገኛ
የጥፋት መመልገኛ
ተመረጠ መሆን አንኛ
ወያኔን ደስ እንዲለው. . .
ሰበብ ይዞ መማለኛ
አወይ አንኛ! ይቺ ጥኛ!
መድረሻዋን እንኛ!
ማደጊያዋን ዕንኛ!።

በአገር ጉዳይ ሲዶለት
መጥፎውን ሁላ መተቸት
አያዋጣም! ይቅር ማለት
ለማፍረስ የራስን ቤት
እንደ "በሌላ ድርጅት መግባት"
ተጠቀሰ እንደ ምክኒያት
ኢሕአፓን ለመምታት
አወይ ክደት! አወይ እብደት::

“መደየን ዕንጂ መኮነን፤
ዕንደ ኩንቲ ዕንደ ጋኔን
በምን ስሌት? በምን ሚዛን?
<u>ተመካኝቶ በአምባገነን</u>
<u>የሰማዕት ደም ማምከን።</u>

ግፈኛን ለማባረር
በፀረ-ወያኔ ግንባር
ሁሉም እንደዕምነቱ ሊመክር
ሲጥር፤ሲጣጣር፤ ሊተባበር
ቆሞ ሳለ የሕዝብ ዛር
ተሰብስቦ በአንድ አኪር
ወያኔን ሲያንጨረጭር
ወያኔም ሲንጨረጨር
አንጃ መጣ ስንክ-ሳር
የሕብረት ጠር፤ጥቁር ጠጠር።

ወያኔ ያለ ሀይሉን
ዓልሞት ባይነቱን
መግረፍ፤መግደል፤ማሰሩን
ዕጁ በደም መበከሉን
ወገን በጠኔ ማለቁን
ቄዬ ለቆ መሰደዱን
ችጋር ግፉ መብዛቱን
ዕያዩ አያዩምን?::

ነበረ ተረቱ
“ካንድ ብርቱ፤ሁለት መዳኒቱ”
ለነፃነት፤ ላርነቱ
ግና!
“ወያኔን ለማውረድ ከሆነ”
ከልብ ካለቀሱልነ
የምን ዉሃ ቅዳ ውሃ መልስ
ነገር ማደባበስ
እቅጩን ንገሩነ
ኢሕአፓ ወያኔ ነው በሉነ!
በጌታቸው ማሩ ወ - ደሙ
በብርሀነ መስቀል ስጋ
ባንጃ ፀሎት ዘክሩነ
አዲስ ቀኖና ስበኩነ
ተዬህ ወዲያ ምን ቀረነ
ወዳጅ ከሰየጠነ።

“መደየን ዕንጂ መኮነን፤
ዕንደ ኩንቲ ዕንደ ጋኔን
በምን ስሌት? በምን ሚዛን?
ተመካኝቶ በአምባገነን
የሰማዕት ደም ማምከን።
በታኞች! አንጃዎች!
የት ነበራቹ?
መቸ ታያቹ
ለስጋቹ ያደራቹ
ለጥፋት ያደራቹ
ካናዳ-ቺካጎ ቦድናቹ
ኤል-ኤንም ጨምራቹ
አትላንታ ላይ ሰረጋቹ
ዲሲ ላይ ፈነዳቹ::

ቸር ይግጠመን